በተለይም ከቅርብ ቀናት ወዲህ እየተወሰደ ያለው የጅምላ እሥራትና ወከባ የችግሩን አሳሳቢነት ያመለክታል፡፡ የአባሎቻችን እሥራትና ማሳደድ በተለይ ተጠናክሮ የቀጠለው ከሐምሌ 2001 ጀምሮ ቢሆንም ከጳጉሜ 3 ቀን 2001 ዓ.ም ወዲህ ያለው ሁኔታ እጅግ አሳሳቢ ሆኗል፡፡ ይኸውም ከላይ ከተጠቀሰው ቀን ጀምሮ በመላ የኦሮሚያ ወረዳዎች የሚገኙ ከ 412 በላይ አባሎቻችንና ደጋፊዎቻችን በተለያዩ እሥር ቤቶች እንዲታሠሩና ቤታቸው እንዲበረበር፣ በታሠሩበትም በማስፈራራትና በማዋከብ በግዳጅ ምንነቱን ያልታወቀ ፎርም ማስሞላትና የጣት አሻራ የማንሳት፣ ለምን አገልግሎት እንደሆኔ የማይታወቅ ፎቶ ግራፋቸውን አስገድዶ የማንሳት ድርጊቶች እየተፈጸሙባቸው ይገኛሉ፡፡ ከዚህም ሌላ ቤተሰብ ምግብ ሊያቀርብላቸው በማይችሉበት ራቅ ያለ ቦታ ላይ እንዲታሠሩ በማድረግ በምግብ እጦት ጭምር እንዲቀጡ እየተደረጉም ያሉ ይገኛሉ፡፡ በተለይ የእሥራቱ ሰለባ እየሆኑ ያሉት በመጪው 2002 ምርጫ ተቃዋሚዎችን በመወከል ለምርጫ ለመወዳደር ይቀርባሉ ተብለው የሚጠረጠሩት ናቸው፡፡ ይህንን መግለጫ በመዘጋጀት ባለንበት ቀን ማለትም መስከረም 8 ቀን 2002 ዓ.ም በምዕራብ ሸዋ በጊንጪ ከተማ አካባቢ ብቻ 12 የኦህኮ አባላትና ደጋፊዎች መታሠራቸውን ለማወቅ ችለናል፡፡ ከዚህም ሌላ የ8ኛና የ10ኛ ክፍል ብሔራዊ ፈተና አጠናቀው ወደ ሁለተኛ ደረጃና መሰናዶ ትምህርት ያለፉት ተማሪዎች የኦህዴድ አባልነት መታወቂያ ካላመጣችሁ አትመዘገቡም ተብሎ እየተከለከሉ ናቸው፡፡

ከተለያዩ ዞኖች በደረሱን ሪፓርቶች መሠረት የታሠሩ አባሎቻችንና ደጋፊዎች ዝርዝር ቀጥሎ ተመልክቶአል፡፡

| | | | |
|---|---|---|---|
| 1. ምዕራብ ሸዋ ዞን | 222 | 10. ፊንፊኔ ዙሪያ | 8 |
| 2. ሰሜን ሸዋ ዞን | 12 | 11. ምዕ/ አርስ | 4 |
| 3. ደቡብ ምዕራብ ሸዋ ዞን | 9 | 12. ምስ/ሐረርጌ | 2 |
| 4. ምስራቅ ወለጋ ዞን | 46 | 13. ምስ/ሸዋ | 7 |
| 5. ምዕራብ ወለጋ ዞን | 33 | 14. ሆ/ጉ/ወለጋ | 18 |
| 6. ጅማ ዞን | 3 | 15. አዲስ አበባ | 2 |
| 7. አርሲ ዞን | 17 | | |
| 8. ቦረና ዞን | 16 | | |
| 9. ጉጂ ዞን | 13 | | |

